# ደንብ

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

***ተዛማጅ መግለጫዎች፡-*** ABA-RB፣ AFA-RA፣ BBB፣ CNA-RA፣ DJA-RA፣ GAA፣ GGA-RA፣ IGK-RB፣ IGT-RA፣ KGA-RA

***የሚመለከተው አካል፡-*** የሰው ሀብትና ልማት ሀላፊ ጽ/ቤት
የአካዴሚ ዋና ሃላፊ
የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻል ዋና ኃላፊ

## *የሠራተኛ የጥቅም ግጭት*

I. ***ዓላማ***

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የላቀ የስነምግባር እና ሙያዊ ብቃት ደረጃ ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው። ይህ ደንብ በሜሪላንድ የስነምግባር ህግ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ BBB፣ ስነምግባር፣ ላይ ከተደነገገው በተጨማሪ የሚጠበቁ ነገሮችን ያስቀምጣል፤ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞችን ስነምግባር በሚመለከት የፍላጎት ግጭቶችን ለማስቀረት እና የጥቅም ግጭት በሚፈጠርበት ጊዜ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎችና መመሪያዎችን ያብራራል።

II. ***ዳራ***

A. ሁሉም ሠራተኞች ከሁሉም ተማሪዎች፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ በሁሉም ደረጃ ከሚገኙ ባልደረቦች፣ እና ከማህበረሰብ ጋር በከፍተኛ አንድነት/ሐቀኝነት እና የሙያ ስነምግባር ግንኙነት እንዲኖራቸው ይጠበቃል።

B. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ስለዚህ ደንብ እና ስለቦርድ ፖሊሲ BBB፣ ስነምግባር፣ እንዲያውቁ እና ይህንን ደንብ እና ፖሊሲ የሚያከብር ባህሪ እንዲያሳዩ እና የእነርሱ ባህርይ እና ተግባሮቻቸው ከቦርዱ ፖሊሲዎች ጋር የሚጣጣም መሆኑን እና የጥቅም ግጭትን እንደማይፈጥር ለማረጋገጥ በራሳቸው ኃላፊነት እንዲወስዱ ይጠበቃል፣ይህንንም የሚያደርጉት የሚከተሉትን ለማሳካት ነው—

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት በከፍተኛ ደረጃ የህዝብ አመኔታ የሚጣልበት አድሎአዊ ያልሆነ ነፃና ፍትኃዊነት የሰፈነበት አሠራርን ለማጎልበት፣ እና

2. ለህብረተሰቡ ግልጋሎት የሚውሉ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረትና ሀብት-ሪሶርሶችን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል።

C. የጥቅም/የፍላጎት ግጭት አለ የሚባለው አንድ ሰራተኛ የሚከተሉትን ሲፈፅም/ስትፈጽም ነው—

1. ከተማሪዎች፣ከወላጆች/ሞግዚቶች፣ከሠራተኞች፣ ወይም ከትምህርት ቤት ሥርአት ጋር ቢዝነስ ከሚሠሩ ከሌሎች አካላት ጋር ያሉ ግንኙነቶችን ለግላዊ ጥቅም ወይም ሌላ ሰውን ወይም ህጋዊ ሰውነት ያለውን አካል ለመጥቀም እንደ ጥቅም ማግኛ እድል አድርጎ መውሰድ፣ ወይም

2. የሥራ ቦታ ኃላፊነታቸውን፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሪሶርሶችን፣እና/ወይም ምስጢራዊ ወይም በትምህርት ሥራ ባላቸው ኃላፊነት ምክንያት የተገኙ መረጃዎችን ለግላዊ ጥቅም ወይም ሌላ ሰውን ወይም ህጋዊ ሰውነት ያለውን አካል ለመጥቀም ማዋል/አሳልፎ መስጠት፣ ወይም

3. ለማንኛውም ኦዲት፣ጥናት ሲደረግ፣ ወይም ምርመራ ሲደረግ ሀሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃዎችን መስጠት።

D. ሠራተኞች የጥቅም ግጭት ይፈጥራል ብለው የሚሰጉበት አግባብ ያልሆነ ባህርይ ካለ በቅድሚያ በይፋ መመሪያ እንዲጠይቁ ይበረታታሉ። በፖሊሲ BBB የስነምግባር ድንጋጌ ላይ እንደተገለጸው፣ማንኛውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተቀጣሪ ወይም ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስራ እጩ የሆነ ሰው ከትምህርት ቦርድ የስነ-ምግባር ፓነል/Board of Education Ethics Panel አስተያየት ሊጠይቅ ይችላል።

E. የጥቅም ግጭቶችን የሚመለከቱ ነገሮች ሁሉም እዚህ ደምብ ላይ በግልጽ አልተጠቀሱም። በዚህ ደንብ ውስጥ በግልጽ ላለተገለጹ ጉዳዮች፣ ወይም የትርጉም ጥያቄዎች ካሉ፣ መመሪያ እንዲሰጥ ጥያቄ የሚቀርብለት አካል የሚከተለው ነው—

1. እንደአግባብነቱ የሠራተኞችን ሱፐርቫይዘር ወይም ርእሰመምህር(ት) ወይም ከዚያም

2. ርዕሰመምህራን ወይም ሱፐርቫይዘሮች ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሏቸው ለሰው ሀብትና ልማት ጽ/ቤት (OHRD) ሀላፊ/ተወካይ፣ ወይም የተነሳው ጉዳይ የቦርድ ፖሊሲ BBB ላይ የተመለከተ ከሆነ በፖሊሲ BBB፣ስነምግባር ላይ በተቀመጡት ሂደቶች መሰረት ለስነምግባር ኦፊሰር (ethics officer)

## III. ትርጉም

A. የቁጥጥር ሰንሰለት ማለት የዕለት ተዕለት ሥራን የመምራት ወይም የመቆጣጠር እና/ወይም ሠራተኛን የመገምገም ወይም ወደ ሠራተኛ ግምገማ የሚያመሩ ምልከታዎችን የማከናወን ኃላፊነት ያለባቸው ሰራተኞች ማለት ነው። የዲስትሪክቱ መሪ የቁጥጥር ሰንሰለት ለእርሱ ሪፖርት የሚያደርጉትን ሰራተኞች እና እነርሱ የሚቆጣጠሯቸውን ሰራተኞች ዝርዝር ያካትታል።

B. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሀብትና ንብረት በህዝብ ገንዘብ ተገዝተው የ MCPS ንብረት የሆኑ እና/ወይም MCPS ሥራ የሚሠራባቸው ንብረቶች፣በዚህ ብቻ የሚወሰን ሣይሆን፣ንብረቶች፣ትምህርት ቤቶች፣ተሽከርካሪዎች፣ የሥራ መሣሪያዎች፣ግብአቶች፣እና የአእምሯዊ ኃብት ባለቤትነት፣ሥርዓተ ትምህርትን ጨምሮ እና/ወይም ሌላ የባለቤትነት መብት ወይም ምስጢራዊ መረጃዎች ማለት ነው።

## IV. የጥቅም ግጭትን ስለ ማስወገድ መመሪያ

A. (ሀ) ከሱፐርቫይዘሮች የሚጠበቁ ነገሮች

1. የመቆጣጠር ወይም የአመራር ሚና ያላቸው ሰራተኞች

a) በቁጥጥር ወይም በአመራር ቦታዎች ላይ ያሉ የ MCPS ሰራተኞች የትዳር አጋርን፣ ዘመድን፣[1] አማችን፣ ወይም ከእሱ/ከእሷ ጋር ጾታዊ/የፍቅር ግንኙነት ያለውን/ያላትን፣ ወይም ባለፉት 10 ዓመታት ውስጥ ጾታዊ/የፍቅር ግንኙነት የነበረውን/የነበራትን ሰራተኛ ያላቸውን የተቆጣጣሪነት ሚና ተጠቅመው መቆጣጠር አይችሉም።

b) አንድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ ነጋዴ ወይም ኮንትራክተር የሆነ/ች የትዳር አጋርን፣ ዘመድን፣ አማችን ወይም ጾታዊ/የፍቅር ግንኙነት ያለውን/ያላትን ማንኛውንም ሰው በተቆጣጣሪነት የኃላፊነት ሚና መቆጣጠር አይችሉም።

c) ሱፐርቫይዘሮች የግል ጥቅም ለማግኘት ወይም ለትዳር አጋር፣ ለዘመድ፣ ለአማች፣ ወይም ከእሱ/ከእሷ ጋር ጾታዊ/የፍቅር ግንኙነት ላለው/ላላት ለማንኛውም ሰው ጥቅም ለማስገኘት ሲባል የተቆጣጣሪነት ሚና ካላቸው ሰራተኞች ጋር ገንዘብ ነክ ግንኙነት አይኖራቸውም።

d) ማሳወቅ ያለባቸው ሁኔታ:-

---

[1] ይኼውም ዘመድ የሆነ የቤተሰብ አባል ወይም ልጅን ይጨምራል።

i) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሱፐርቫይዘሮች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ወይም ኃላፊነት የተሰጣቸው መሪዎች የትዳር አጋሮቻቸውን፣ዘመዶቻቸውን፣ አማቾቻቸውን፣ ወይም ከእርሱ/ከእርሷ ጋር ጾታዊ/የፍቅር ግንኙነት ያላቸውን፣ ወይም ባለፉት 10 ዓመታት ውስጥ ጾታዊ/የፍቅር ግንኙነት የነበራቸውን ሰው የሚቆጣጠሩበት ሁኔታ ከተፈጠረ፣ ለቅርብ ሱፐርቫይዘራቸው ማሳወቅ አለባቸው፣ የቅርብ ሱፐርቫይዘራቸውም ሁኔታውን ለ OHRD ሀላፊ/ተወካይ ማሳወቅ ይኖርበ(ባ)ታል።

ii) ከዚያ በኋላ የቁጥጥር ኃላፊነቱ ለሌላ ተቆጣጣሪ እንዲሰጥ የማድረግ ኃላፊነት በሚመለከተው የሥራ አስፈፃሚ አባል ይወሰናል፣ወይም በትምህርት ቤቱ ወይም በጽ/ቤቱ ፍላጎት ላይ በመመስረት ከሠራተኞቹ መካከል አንዱን ወደሌላ ቦታ መመደብ ይቻላል።

iii) ለቁጥጥር ወይም ለአመራር ቦታዎች እጩ ሆነው የተመረጡ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ከእርሱ/ከእርሷ ጋር ጾታዊ እና/ወይም የፍቅር ግንኙነት ያለውን/ያላትን፣ ወይም ባለፉት 10 አመታት ውስጥ ጾታዊ እና/ወይም የፍቅር ግንኙነት የነበረውን/የነበራትን ሰው የሚቆጣጠሩበት ሁኔታ ከተፈጠረ ሁኔታውን ለ OHRD ሀላፊ/ተወካይ ማሳወቅ አለባቸው። ከላይ IV.A.1.d.ii ላይ እንደተገለጸው ምክንያታዊ እርምጃዎች ከተወሰዱ እንደዚህ ዓይነቱን ሁኔታ ማሳወቁ/ቋ እጩውን/ዋን ለሥራ መደቡ ከመመረጥ አያግድም።

B. (ለ) በትምህርት ቤት የሚማሩ የሠራተኞች ልጆች

1. የአንድ ተማሪ ቋሚ መኖሪያ ትምህርት ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ ክልል ከሆነ፣(COSA) የትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ የፀደቀለ(ላ)ት ከሆነ፣ ወይም ትምህርት ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ ክልል ነዋሪ ሳይሆን/ሳትሆን እንዲገባ/እንድትገባ የተፈቀደለ(ላ)ት እና የትምህርት ክፍያ ተከፍሎ ከሆነ ወይም እንዳይከፈል የተተወሰለ(ላ)ት ከሆነ ብቻ ተማሪ ው(ዋ) ወላጅ ወይም ዘመድ በሚሰራበት/በምትሰራበት ት/ቤት መከታተል ይችላል/ትችላለች። እንደዚህ አይነቱ ጥያቄ ሊፀድቅ የሚችለው ሌላ አማራጭ ከሌለ እና የጥቅም ግጭት በሌለው ሱፐርቫይዘር አማካይነት ከተወሰነ ብቻ ነው።

2. በተቻለ ጊዜ ሁሉ፣ በሠራተኛው(ዋ) እና በልጅ መካከል እንዲሁም ከሠራተኛ የሥራ ኃላፊነት መካከል የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ ማናቸውንም ሊሆን የሚችል ወይም የሚታሰብ የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ ስለ ተማሪው(ዋ) ውሳኔ ወይም ሙያዊ ግብአት የመስጠት ኃላፊነትን ወደ ሠራተኛው(ዋ) የቅርብ ተቆጣጣሪ ማስተላለፍ ይገባል።

3. ሌላ አማራጭ ካልኖረ በስተቀር ልጁ/ልጅቱ ወላጅ/ሞግዚት ወይም ዘመድ በሚያስተምሩበት ክፍል መመደብ የለበ(ባ)ትም። ሌሎች አማራጮች ከሌሉ፣ ሠራተኛው(ዋ)፣የእርሱ(ሷ) ሱፐርቫይዘር፣እና ከትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ጋር ለልጁ/ለልጅቷ ዕቅድ ይዘጋጃል።

C. ሰዎችን፣ ገንዘብ፣ ንብረት፣ ወይም ሌላ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት/ሪሶርሶችን ለግል ጥቅም ማዋል

1. ማንኛውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች በሃላፊነት የሚቆጣጠሩትን ወይም የሚመሩትን ወይም የሚያስተዳድሩትን ማንኛውንም ሰው፣ገንዘብ፣ንብረት፣ወይም ሌላ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሪሶርሶችን ለግላቸው የጥቅም ማግኛ፣ወይም ለሌላ ግለሰብ ወይም ለሌላ ህጋዊ ሰውነት ላለው አካል መጠቀሚያ አይደረግም። ሠራተኞች አልፎ አልፎ ወይም በውስን ሁኔታ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እቃን/መሳሪያን ወይም ፋሲሊቲን በግል መጠቀም ይችላሉ፤ ነገር ግን ይህ የሚሆነው—

a) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) ንብረት አጠቃቀሙ እምብዛም ግምት ዉስጥ የማይገባ ወይም ወጪ የማያስወጣ ከሆነ፣

b) አጠቃቀሙ ከሠራተኛው(ዋ) መደበኛ ሥራ ጋር የማይጣረስ ወይም በሌላ ሠራተኛ መደበኛ የሥራ አፈጻጸም ላይ ጣልቃ የማይገባ/ የማይጋጭ ከሆነ፣እና

c) አጠቃቀሙ ከማናቸውም የቦርድ መርህ ወይም MCPS ደንብ ጋር የማይጋጭ ከሆነ።

2. ከዚህ ቀደም በከዲስትሪክት ኦፕሬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ/ተወካይ የተደረገ ስምምነት ከሌለ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተሽከርካሪዎች ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) ሥራ በሚሰሩበት ጊዜ ብቻ ነው። ሌሎች ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ አገልግሎት ብቻ የሚውሉ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መሣሪያዎች የሚያካትቱት፣ ማሽኖች፣ የፅዳት እና መቀቢያ መሣሪያዎች፣ እና በአገልግሎት የሚያረጁ መሣሪያዎች በሙሉ ናቸው።

D. ስራ

1. የዉጪ ሥራ/ከሥራ ቀን ውጭ መሥራት

a) አጠቃላይ-የስራ ሀላፊነታቸውን ለመወጣት ሁሉም የሙያ ሠራተኞች ከመደበኛው የሥራ ቀን በተጨማሪ የተወሰኑ ሰዓቶችን እንዲሰሩ የሚጠበቅባቸዉ መሆኑ ይታወቃል። እነዚህ መስፈርቶች በማንኛውም ጊዜ ቅድሚያ ይኖራቸዋል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) የሥራ ኃላፊነት ለመወጣት በማይጠበቅባቸው ሠዓቶች እና የቦርድ ፖሊሲ BBB የማይጥስ የውጭ ሥራ መሥራት የጥቅም ግጭት ተደርጎ አይቆጠርም።

b) በትምህርት ቤት የሚሠሩ-የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ከትምህርት ቤት ጋር የተገናኙ ሥራዎችን ለመሥራት በተመደቡበት ትምህርት ቤት(ቶች) በመማር ላይ ለሚገኙ፣ወይም ለሚከታተሉ ተማሪዎች ወላጆቻቸው ገንዘብ መክፈል ያለባቸው፣አግባብነት ባለዉ መጠን አበል የሚከፈለው ከቦርዱ ካልሆነ በስተቀር ከሌላ ድርጅት ክፍያ መቀበል የለባቸውም። ይህም የሚያካትተው በዚህ ብቻ የሚወሰን ባይሆንም፣ ድራማ፣ዳንስ፣ወይም የሙዚቃ ትምህርt ወይም ሥራዎችን ያጠቃልላል።

c) ከትምህርት ቤት ሥራ ጋር የማይገናኙ፡-ተግባሩ ከትምህርት ቤቱ ጋር የማይገናኝ ከሆነ እና ሰራተኛው(ዋ) በተመደበ(ች)በት ት/ቤት ከትምህርት ሰዓት በፊት ወይም በኋል የሚካሄድ ከሆነ፣እና ወላጆች ለዚያ ተግባር መክፈል ያለባቸው ከሆነ የ MCPS ሠራተኛ በተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት የሚማሩ፣ ወይም ይማራሉ ተብለው የሚጠበቁ ተማሪዎችን ማስተማር የለባቸውም።

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) የትምህርት ተልእኮ በሚደግፉ የውጭ አጋር ድርጅቶች መካከል ከሚደረግ ሥምምነት ጋር በሚጣጣም መልኩ፣በዚህ ሥራ ላይ ያለ(ች) ሠራተኛ ተማሪዎቹ በሚሠማሩበት ፕሮግራም የማይሣተፍ-የማትሣተፍ ከሆነ እያንዳንዱ ጉዳይ እየታየ በሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ አማካይነት ሊወሰን ይችላል።

2. የእረፍት ጊዜ ሥራ

በክፍያ ወይም ያለክፍያ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በእረፍት ላይ ያለ(ች) ሠራተኛ፣ በእረፍት ላይ በሚሆንበት-በምትሆንበት ወቅት ከዋና የሥራ ኃላፊ በጽሑፍ ካልተፈቀደ

በስተቀር በማናቸውም ደረጃ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሥራ እንዲሠራ-እንድትሠራ አይቀጠርም-አትቀጠርም።

3. በግል ማስጠናት እና የሠመር ካምፖች

a) ለብቻ የትምህርት ክፍለ ጊዜ/በግል አስተማሪ የሚሰጥ ትምህርት

በግል ማስጠናት ማለት ከመደበኛ የትምህርት ቀን ውጪ በክፍያ የሚካሄድ ተጨማሪ፣ልዩ፣ ወይም የማሚያ ማስጠናት/ትምህርት መስጠት ነው። (በተጫማሪ MCPS ደንብ ABA-RB፣ ስለ ትምህርት ቤት ጎብኚዎች/School Visitors) ይመልከቱ

(1) በግል የማስጠናት ተግባር መደረግ ያለበት ከሠራተኛ የሥራ ሠዓት ውጪ ነው።

(2) የ MCPS ሠራተኛ በሚሠራበት-በምትሠራበት ትምህርት ቤት የሚማር/የምትማር ወይም ይ(ት)ማር ይሆናል ተብሎ የታሰበ ተማሪን በግል አያስተምርም፣ አያስጠናም፥ አታስተምርም፣ አታስጠናም።

(3) እንደ ጉዳዩ ሁኔታ አንድ በአንድ እየታየ በሱፐርኢንተንደንቱ/ተወካዩ አማካይነት ተቀባይነት የሚሰጣቸው ልዩ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላል —

(a) ልዩ ሙያተኞች ለሚያስፈልጓቸው እክል ላለባቸው ልጆች የሚሰጡ የሠመር ፕሮግራሞች ሲኖሩ እና የልዩ ሙያተኞች እጥረት ባለበት ሁኔታ፣ በሠመር እንዲያስጠኑ ከወላጅ/ከሞግዚት በጽሑፍ የቀረበ ጥያቄ በትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻል ጽ/ቤት ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ፣የልዩ ትምህርት ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ፣እና በርእሰመምህር ሲፀድቅ፣ ወይም

(b) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) የትምህርት ተልእኮ በሚደግፉ የውጭ አካላት ጋር ከሚደረግ የጋራ ሥምምነት መርሆዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ፣በማስጠናት ሥራ ላይ ያለ(ች) ሠራተኛ ተማሪዎቹ ወደሚሠማሩበት ፕሮግራም ሂደት ላይ የማይሣተፍ-የማትሣተፍ ከሆነ።

(4) ወደ MCPS ፕሮግራም ለማስገባት ተማሪዎችን ለፈተና እንዲዘጋጁ ሠራተኞች በማስጠናታቸው ምክንያት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ (MCPS) አካል ካልሆነ ድርጅት ወይም ግለሰብ ማካካሻ አይቀበሉም።

(5) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ (MCPS) ሠራተኞች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ንብረት ላይ የማስጠናት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልጉ ከሆነ፣ ይህንን ደንብ "MCPS ደንብ KGA-RA" መከተል ይኖርባቸዋል የማህበረሰብ የፐብሊክ ስኩልስ ንብረት አጠቃቀም።

b) የሠመር ካምፖች እና ከትምህርት ሠዓት በፊት ወይም በኋላ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች

በትምህርት ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ የሠመር ካምፖች እና ከትምህርት ሠዓት በፊት ወይም በኋላ ስለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች

ሠራተኞች እነዚህን መመሪያዎች መከተል ይኖርባቸዋል:- የሠመር ካምፖችን/ፕሮግራሞችን/እንቅስቃሴዎችን ለሚያካሄዱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ መመሪያ - እና ተፈጻሚነት ያላቸውን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የአትሌቲክስ መመሪያ/MCPS Athletic Handbook እናእና

የሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአትሌቲክ ማህበር መመሪያ/Maryland Public Secondary Schools Athletic Association Handbook።

(2) በትምህርት ቤት ስፖንሰር የማይደረጉ የሠመር ካምፖች እና ከትምህርት ሠዓት በፊት ወይም በኋላ የሚደረጉ ተግባሮች/እንቅስቃሴዎች:-

(a) ሰራተኞች በሚያስተምሩበት፣ በተመሳሳይ ስፖርት ቡድን ውስጥ በሚያሰለጥኑበት፣ ወይም በማንኛውም ለውድድር በሚመረጥ ቡድን ውስጥ የሚካተቱ የተማሪ አባላትን በመምረጥ ላይ በሚሳተፉበት ትምህርት ቤት ውስጥ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ፣ ወይም ትምህርታቸውን ይከታተላሉ ተብለው የሚታሰቡ/የሚጠበቁ ተማሪዎችን በየትኛውም የስፖርት ካምፕ ወይም በክህሎት ማሠልጠኛ ካምፕ፣ወይም ከትምህርት በፊት ወይም በኋል በሚከናወኑ ተግባሮች/እንቅስቃሴዎች ውስጥ ማስተማር የለባቸውም።

(b) ሠራተኞች የትምህርት ቤት ንብረት/ፋሲሊቲን ወይም የትምህርት ቤት ሜዳዎችን ለመጠቀም በማህበረሰብ የንብረት/የፋሲሊቲ አጠቃቀም በኩል ማመልከት ይኖርባቸዋል።

(c) ሁሉም ማህበረሰብ እንዲጠቀምበት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር ሠራተኞች የትምህርት ቤትን መገልገያ መሣሪያዎች እና አቅርቦቶችን መጠቀም አይኖርባቸውም።

E. ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት

በሠራተኛ አማካይነት የፈጠራ ውጤቶች-የሚሠሩ-የሚዘጋጁ አቅርቦቶች፣ የሥራ መሣሪያዎች፣ ወይም እቃዎች/ቁሳቁሶች

1. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚከናወን ግዢ

ሠራተኞች ከተቀጠሩበት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሥራቸው እና ኃላፊነታቸው ጋር ምንም አይነት ተያያዥነት ሳይኖር እና ምንም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን ሪሶርሶች፣ ጊዜ፣ወይም ማቴሪያሎችን ሳይጠቀሙ በግላቸው የሠሯቸውን/ያመረቷቸውን አቅርቦቶች፣መሥርያ መሣሪያዎች፣ወይም ማቴሪያሎች/ቁሳቁሶች ማንኛውንም ለሌላ እቃ ግዢ የሚደረገውን አሠራር መሠረት ባደረገ ሁኔታ MCPS ሊገዛ ይችላል።

a) የሠራተኛ የፈጠራ ሥራ ውጤት አቅርቦቶች፣ የመሥሪያ መሣሪያዎች፣ወይም ቁሳቁሶች-ማቴሪያሎች የቦርድ ፖሊሲ BBB፣ ሥነምግባር እና ሌሎች በሥራ ላይ ያሉ የአሠራር ደንቦችን መሠረት በማድረግ ለግዢ መመረጥና መፅደቅ አለባቸው።

b) እቃው በሥራ ላይ ያለ(ች) ወይም የቀድሞ የሥራ ባልደረባ የፈጠራ ሥራ ውጤት በመሆኑ እንዲመረጥ ወይም እንዳይመረጥ ምክንያት መሆን የለበትም።

2. የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ፣ሠራተኞች የትዳር ጓደኞቻቸው፣ ዘመድ፣አማቾች፣ወይም ማንኛውም የጾታ ግንኙነት ካላቸው ሰው ግላዊ ጥቅም ከሚያስገኝ ማናቸውም አይነት የግዢ ውሳኔዎች፣ ምርጫ ማከናወን፣ ወይም ሌላ ውሳኔ የመስጠት ሒደቶች ራሳቸውን ማግለል አለባቸው።

3. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት

a) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን ጊዜ፣ ፋሲሊቲዎችን፣ ቁሳቁሶችን፣ወይም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሪሶርሶችን በመጠቀም ወይም የሠራተኛው(ዋ) የሥራ ድርሻ-ሃላፊነት ጋር በተያያዘ ምክንያት በአንድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሠራተኛ በተናጠል፣ወይም ከሌሎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሠራተኞች ጋር በህብረት የፈጠራ ችሎታ የተዘጋጁ አቅርቦቶች፣የመሥሪያ መሣሪያዎች፣ወይም ማቴሪያሎች-ቁሳቁሶች ንብረትነታቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ይሆናል።

b) ሥራው/ተግባሩ በከፊል የግል እና በከፊል የህዝብ በሚሆንበት ሁኔታ፣ፈጠራውን ላከናወነው(ችው) ሰው የሚከፈለው ክፍያ ቢከፈልም ባይከፈልም፣ OHRD ዋና የሥራ ኃላፊ/ተወካይ አማካይነት የቅድሚያ ዝርዝር ስምምነት መፅደቅ ይኖርበታል።

F. የባለቤትነት መብት ወይም ምስጢራዊ መረጃዎችን ስለመጠቀም

1. ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ሃላፊነት ምክንያት የያዘ(ች)ውን የተማሪዎችን እና/ወይም የወላጅ/የሞግዚት መረጃ ዝርዝር MCPS ደንብ JOA-RA፣ የተማሪ ሪከርድ፣ እና MCPS ደንብ AFA-RA፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የምርምር እና መረጃ ማሰባሰብ አካል የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር ለማንኛውም ሌላ ሰው ወይም የንግድ ድርጅት አሳልፎ መስጠት አይችልም-አትችልም።

2. ሠራተኞች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኛ በመሆናቸው ምክንያት የሚያገኙትን ለህዝብ ይፋ ያልተደረጉ ድርጅታዊ መረጃዎችን መግለጽ ወይም መጠቀም አይኖርባቸውም። ማንኛውም ልዩ ሁኔታዎች OHRD ዋና ኃላፊ/ተወካይ በቅድሚያ በጽሁፍ መፈቀድ አለባቸው።

## V. ደንብ አለማክበር-ጥሰት

ይህንን ደንብ የመጣስ ሁኔታ አለ ተብሎ ከተጠረጠረ OHRD ዋና ኃላፊ/ተወካይ አማካይነት አስቸኳይ ምርመራ ለማድረግ ምክንያት ሊሆን ይችላል። አንድ ሰራተኛ ይህንን ደንብ እንደጣሰ(ች) ከተረጋገጠ፣አግባብነት ያላቸው ህጎች፣ የቦርድ ፖሊሲዎች፣ MCPS ደንቦች፣ እና MCPS የሠራተኛ ስነምግባር ደንብ በሚፈቅደው መሠረት ሠራተኛው(ዋ) የተግሣጽ እርምጃን፣ እገዳን፣ ወይም ከሥራ የመሰናበት እርምጃን ጨምሮ የዲስፕሊን እርምጃ ሊወሰድበ(ባ)ት ይችላል።

***ተዛማጅ የመረጃ ምንጮች፡-*** Annotated Code of Maryland, Maryland Public Ethics Law Article, Subtitle 8; Code of Maryland Regulations, §13A.06.03.04.G; MCPS Employee Code of Conduct; Handbook of the Maryland Public Secondary Schools Athletic Association; Guidelines for Montgomery County Public Schools Conducting Summer Camps/Programs/Activities

**ስለ ደንቡ *ታሪክ*፡-** አስቀድሞ ደንብ ቁ. 490–1፣ ዲሴምበር 29,1978 (የማውጫ መረጃው ተሻሽሏል)፣ ኖቬምበር 16, 2000 ተሻሽሏል፣ ኤፕሪል 9, 2002 ተሻሽሏል፣ ኤፕሪል 17, 2013 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 31, 2017 ተሻሽሏል፣ ኦገስት 15፣ 2024 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድጅንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-
U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, ዐወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org